# በዐማራ አካባቢ የነበሩ የሥርዓቱ ደጋፊዎች ንብረቶቻቸውን እየሸጡ እየወጡ ነው

**(ሙሉቀን ተስፋው)**

በዐማራ አካባቢ የነበሩ የሥርዓቱ ደጋፊዎች ንብረቶቻቸውን እየሸጡ እየወጡ ነው፤ በባሕር ዳር ሐዳስ ወደ አዲሴ ተቀይሯል!

በተለያዩ የዐማራ ‹ክልል› አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ የትግራይ ተወላጅ የሥርዓቱ ደጋፊዎች ቤታቸውን እየሸጡ እየወጡ ነው፡፡ የቤትና ንብረት ሽያጭ ከደራባቸው ከተሞች መካከል ጎንደር፣ ወልዲያ፣ ባሕር ዳርና ደሴ ዋናዎቹ ናቸው ተብሏል፡፡

የዘረፉትን ገንዘብ እየሸጡ የሚወጡ የሥርዓቱ ደጋፊዎች የሚገዙ ባለሀብቶች ተባባሪ መሆን እንደሌለባቸው ያነጋገርናቸው ምንጮች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሸጠው ከወጡት ግለሰቦች መካከል የቡሬው አቶ በርሄ ይገኙበታል፡፡ አቶ በርሄ የትንሳኤ ሆቴል ባለቤት ሲሆን በ2008 ክረምት በነበረው ተጋድሎ 6 ያክል ሰዎች ተገድለው በሆቴሉ የተገኙበት ግለሰብ ነው፡፡

መሸጥ ያልቻሉ ግለሰቦች የንግድ ተቋሞቻቸውን ስማቸው እየቀየሩ ነው፡፡ ለምሳሌ በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 4 ያለው ‹የሐዳስ መኝታ ቤት› ወደ ‹አዲሴ መኝታ ቤት› ተቀይሯል፡፡ የሐዳስ ወደ አዲሴ በመለወጥ በሥም ቅያሬ ከሕዝብ መደበቅ እንደማያመልጡ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡